# ማን ያውራ የነበረ 8

ዛሬ ሀገራችንን ኢትዮጵያን እየዘረፉና እያደሙት ያሉት ቀዳማይ እመቤት ተብለው ሊሞገሱና ጉዲት የሆኑት ሚኒስቴር ተብለው ተሹመው መድረክ ሊያጣብቡ ሲሞክሩ ማየት ብንገደድም የኢትዮጵያ ሴቶች በታሪክ የተመዘገቡት በጀግንነታቸውና ለእናት ሀገራቸው ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅዖ በማድረጋቸው ነው፡፡ ዛሬ በሁሉም መስክ የታሪክ አተላዎች አለን አለን እያሉ ቢያስቸግሩም  ሀቅንመሰረት የቀደረገው ታሪክ በሚፃፍበት ወቅት ግን ለሁሉ ግልፅ የሚሆነው ሀቅ እናቶቻችንና እህቶቻችን ለዚች በደል ለበዘባባት ሀገር ያደረጉት ሁለ ገብ ትግልና የከፈሉትም ከፍተኛ መስዋዕትነት ይሆናል፡፡ ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ከ1964 ዓ.ም. ጀምሮ <u>የሴቶች ጥያቄ</u> በፖለቲካው ትግል ሊኖረው የሚገባውን ቦታ በመስጠት ታግሏል፡፡ ዛሬም ይህ ትግሉ ግብን አልመታምና በማያወላውል መንገድ ቀጥሎበታል፤ቀጥሏል፡፡

የሴቶች ጥያቄ ብሎ ኢሕአፓ ሲታገል የሕዝብ ገማሽ አካል የሆኑት ሴቶች መብትን በተመለከተ የሚድርሰባቸውን ዘግናኝ በደል በማስወገድ መብታቸውን ማስከበር-ማረጋጋጥ ያስፈልጋል በሚል ነው፡፡ ሴቶች ገማሽ ሰማይን ተሸክመው የያዙ ናቸውና ተበድለው እምቢኝ ካሉ ሰማይ ይደረመሳል በሚል አነጋገር ያቀረቡት ቻይናውያን የአንድን ሀገር ወሳኝ ዜጋ መብት ነፍጎ ሀገር አለ ዴሞክራሲ አለ ማለቱ የማያዋጣ ባልት መሆኑን ለመግለፅ ነው፡፡ ሴቶች የሀገሪቷ ሁለገብ ምሰሶ ሆነው ሳለ በመደባቸው ብቻ ሳይሆን በፆታቸው በተለይ አፀያፊ ጭቀና ይደርስባቸዋል፡፡ አብዛኛው ዜጋ በጨቋኝ ስርዓት ይበደላል ብንልም ሴቶች ደግሞ በፆታቸው የተነሳ የአጠቃላዩ የወንድ ትምክህት ሰለባ ሆነው ድርብ ድርብርብ በደልና ጭቆና ይደርስባቸዋል፡፡ የሴቶችን በደልና ብሶት አድመጠናልና ለለውጥም ተሰልፈናል የሚሉና በወነዶች የበላይነትን ስር ያሉ ድርጅቶች ራሳቸው ሳይቀሩ ለሴቶች ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ የአንገት በላይና ባዶ መሆኑን ደጋግመን አይተናል፤ታዝበናል፡፡ ወያኔን ብንወሰድ አርሶ አደር ሴት በሬ ጠምዳ ስታርስ በፎቶ አንስቶ እነሆ ሴት ልጅ ነፃ ሆነች፤ ከወንድ እኩል ሆነች ብሎ ሊያወናብድ ቢጥርም/የሴት እኩልነት የወንድን ስራ በመስራት ብቻ የሚከሰት ይመስል!/ በድርጅቱ ሆነ በአገዛዙ የሴቶች ቦታ ተጋደልቲ ሆኖ ጭዳ ከመሆን ባሻገር ኢምንት ነው፡፡ ቀዳማይ እመቤተ ተብየዋም ብትሆን ሴቶችን ጭራሽ ካለመወከሏ ሌላ ኃይሏ በላቤቷ መሆኑን ማንም አይስተውም፡፡ ዛሬ ተቃዋሚ ድርጅት ነን የሚሉት ሁሉ--ኢሕአፓንም ጨምሮ-- የወንዶች ክበብ ናቸው፡፡ በድርጅቶች የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው፡፡ መድረኩንና አለ የተባለውን ስልጣን የያዙት ወንዶች ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ ደግሞ ለብዙዎቹ የሴቶቸች ጥያቄ የትግላቸው መፈክር አይደለም፡፡

ኢሕአፓ የሴቶችን ጥያቄ ተገቢውን ሚዛ  ሰጥቶ ትግል ሲያካሂድ ወጣት ሴቶች የጥናት ክበብ ዙሪያ ተደራጅተው ለጥቆም የራሳቸውን ማህበር እንዲያቋቁሙ በማበራታታት ነበር የጀመረው፡፡ በየካቲት አብዮት ጊዜም የሴቶች አስተባሪ ኮሚቴን በመመስረት የሴቶችን የመብት ትግል ለማጠናከር የአቅሙን ጥሯል፡፡ ኢሕአፓ የሴቶች ትግል በወንዶች ሞግዚትነት የሚካሄደ ነው ብሎም ስለማያምን  ሴቶችን በመቀስቀስነቀ በአጠቃላዩ ትግል በማሰለፍ የነቁትና የተደራጁት ሴቶች እህቶቻችውንና እናቶቻቸውን የማደረጃትና የማታገሉን ግዳጅ በቅድሚያ እንዲሸከሙ አድረጓል፡፡ ኢሕአፓ የሴቶችን ድርብ ጭቆና ማወቁ የመጀመሪያው እርምጃ ነበር፡፡ ሴቶች በፆታቸው እየደረሰባቸው ያለውን በደል ቦታ ባለመስጠት ሁሉም ነው የሚበደለው በሚል ሸፋን የሴቶችን የመብት ጥያቄ ወድ ጎን የሚያደርጉ ብዙ ናቸው፡፡ ሴቶች በራሳቸው የመደራጀታቸውን መብትና አስፈላጊነቱንም ኢሕአፓ ቢቀበልም ሌሎች ደግሞ ሴቶች በአጠቃለዩ በሚታገል ድርጅት ውስጥ መኖራቸው ይበቃል በሚል የወንዶችን--ተራማጅ ነን ባዮቹን ጨምሮ- ትምክህት ሸፋፈነው ያልፉታል፡፡ በሀገራችን ቀርቶ ባበዕድም ቢሆን ሴቶች ከነዓነት ደማቸውን አፍሰው የተባለው ሀገራዊ ነፃነት ሲገኝ ግን ሴቶች ከጭቆና ቀደ ጭምና ከመሽጋገር ሌላ መብታቸውን አለማግኘታቸውን አይተናል፡፡ ኢሕአፓ የተቀበለውን እስከተወሰነ ደረጃም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋገጠው ሌላ አቢይ ጉዳይ የሴቶች ድርጅት አንፃራዊ ነፃነት እንዲኖረው ያሻል የሚለውን መርህ ነው፡፡ አኢሴማ ወይም ወያኔ የሚቀጣጠረው የሴቶች ማህበር ዓይነት ሳይሆን ነፃ የሆነና ሴቶችን የሚወክል ሴቶች የሚቆጣጠሩት የሴቶች ድርጅት መኖሩ ወሳኝ ነው፡፡ ወንዶች ወይም አገዛዙ የሚቆጣጠሩት የሴቶች ድርጅት በመሰረቱ የወንዶች ድርጅት ውይም መሳሪያ ነው፡፡

የሴቶች ጭቆና በጥቅሉ በሁሉም ዜጋ ላይ በሙደርሰው ጭቆና ውስጥ ገብቶ ሊገለፅ የሚችል አይደለም።ከበርቴውም ሆነ አርሶ አደሩ ወንድ በወንድነቱ ሴቶችን በተመለከተ የበላይነትን ይዞ በደል ይፈፅማል። በእምነቶችም ደረጃ የሴቶች ቦታ ዝቅተኛ ተደርጎ መቀመጥ ያለ ነው። ታሪክም ቢሆን አልፎ አልፎ ጣይቱ ቢልም የሴቶችን ደማቅ ሚና ከቶም አያወሳም ብንል ማጋነን አይሆንም። በሀገራችን ያሉትን ልዩ ልዩ ባህሎች ብንመረምር ደግሞ ብዙ ፀረ ሴት የሆኑት ልምዶች ባባህል ሽፋን መቀጠላቸውን እናያለን። አቅመ ሄዋን ያልደረሰችውን መዳር፣ የፈርያናውያንን ግርዛተ በጭላ ወይም በከፊል መፈፀም፣መጥለፍ፣መድፈር፣አካሏን ማበላሸት፣ ወዘተና በትምህርትና በስራ መስክም እኩልነቷን አለማስከበር ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። በሀይማኖት ሽፋንም የሴት ልጅ መብት ይረገጣል። ዛሬ በሀገራችን የሴቶችን ቦታና ሚና በሚገባ ብንመረምር የዚህ በደልና ልዩነት ሀቅነት ግልፅ ይሆንልናል። ዛሬ በሀገራችን የዕድገትም ሆነ የዴሞክራሲ ጥያቄ ሲነሳ የሴቶች መብት አለመከበር አለ የሚባለው ዴሞክራሲ መትሀት መሆኑን፣ ባዶ መሆኑን ያሳየ ል። የሴቶች ጭቆና የሰፈነበት ህብረተሰብ ከዴሞክራሲ የተገለለ ህብረተሰብ ነው።

ስለዚህም የሴቶች ጥያቄ ራሱን የ ለ ግን መላ ህበረተሰቡም የሚመለከት ጥያቄ ነው በሚል ኢሕአፓ ሴቶች በትግሉ ተልፈው ለመብታቸውም ለሀገር ነፃነትም አንዲያገሉ ሲቀሰቅስ ቆይቷል። ሀገራችንን ሊጎዳና ሊወር የመጣውን ጠላት ሁሉ ለመቋቋም በተደረጉ ትግሎቸ ሴቶች ገድላቸወ በስፋት ባይወሳም ሚናቸው ቀላል አልነበረም። በየካቲት አብዮት ወቅትና ከዚያም በኋላ ሴቶች ግንባር ወደም ሆነው አረመኔውን አገዛዝ ታግለዋል። በኢሕአፓም ተደራጅተው በከተማውም ሆነ በገጠሩ የትጥቅ ትግል አኩሪ ታሪክ ፅፈዋል። የባህል ገመድ ተብትቦ ሳያፍናቸው ተነሽ ጭቁን ሴት ብለው በድፍረት በትግሉ ገብተወ የከፈሉት መስዋዕትነት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በሴቶች ተሳትፎ ትግል ምን ያህል ሊጎመራ ሊጎለብት እንደሚችልም አሳይተዋል። በተካሄደው ረጅም ትግል የሴቶች ሁኔታ የመሻሻልን ገፅ ያያ ቢሆንም ዛሬም ቢሆን ግን ብዙሀኑ የኢትዮጵያ ሴቶች የእኩልነት መብታቸው አልተከበረም። የህግ ዋስትና በበቂ አላገኙም፣ሲበደሉም ፍትህ ትርቃቸዋለች። በአገዛዙም በወንዱም ይበደላሉ። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ዛሬም ቢሆን የፖለቲካ ፕሮግራሙ አንዱ አቢይ ነጥብ የሴቶችን ጥያቄና የእኩልነት መብት የሚመለከት የሆነው። ሴቶች በሁሉም መስክ ማለትም በስራ፣በትምህርት፣ በመሰራተዊ መብት ደረጃ ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው አንድ ዜጋ መብታቸው ታውቆና ተከብሮ መገኘተ አለበት። ይህም በልፈፋ ደረጃ ወይም በሰነድ ተፅፎ የሚሻግት ሳይሆን በገቢር መዋል ያለበት መርህና ድንጋጌ ሆኖ መገኘት አለበት። የጋብቻ ህግ፣የሴቶች መብትን በተመለከተ የሚወጣ ልዩ ህግ ወዘተ በስራ መዋል መከበር አለባቸው። በሴቶች ላይ የሚደርሰው የአካልና የመንፈስ ጉዳት፣ በደልና ግፍ ሁሉ መቆም አለበት ማለት ነው። ግፍ ፈፃሚዎችና አድልዎን አስፋኞች ደግሞ በህጉ መሰረት ሊቀጡ ይገባቸዋል። አርሶ አደሯ ወይም የገጠሯ ሴት በቅድሚያ በኤኮኖሚ መስኩም ጭምር መብቷን እንዳታስከብር ማድረግ ያሻል። ሴቶች በሀገራቸው የዛሬና የነገ ሁኔታና ዕጣ ላይ ደማቅ፣ቀጥተኛና የራሳቸው ነፃ ተሳትፎ አንዲኖራቸው ማድረግ ድግሞ የግድ ነው። ይ/ሀመብታቸውን የማስከበሩ ሂደት ደግሞ ወሊድንም የመቆጣጠርና የአካላቸውም ባለቤት የመሆንን መብት ይጠቀልላል። የሴቶችን መሰረታዊ መብቶች የሚቃወሙ እምነቶችና ልምዶችን በተመለከተ ኢሕአፓ ሰልፉ ትላንትም ዛሬም ከሴቶች ሙሉ መብት ጎን ነው።

ዛሬ የትግላችን መድረክ ለዴሞክራሲ ቆመናል እያሉ በተጨባጭ ግን ከፀረ ዴሞክራሲና ኋላ ቀር አቅዋማቸው ባልተላቀቁ ግለሰቦች ቢጣበብም ይህ ዳዴ እያለ ያለው ሕዝባዊ ትግል ጥንካሬን ያገኝ ዘንድ የሀገራችን ሴቶች በትግሉ መሰማራት አለባቸው። ሴቶችን በትግሉ ማሳትፍ ካልተቻለ ትግለ ተብዬው መጨረሻው አሁን እያየ ካለነው “እንጎንበስ ለወያኔ” የባሰና አሳዛኝ ይሆናል። ድርጅቶች ይሁነኝ ብለው ሴቶችን ወደ ትግሉ ለመሳብ መጣር ይኖርባቸዋል። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ትግሉ ወደፊት መሄድና ግቡን ማግኘት አይችልም። የሴቶችን ተሳትፎ እውን ማደረግ ያለብን ለትግሉ አሸናፊነት ዋስትና በመሆኑ ሲሆን ሴቶች ግን ለጋራው ትግል ተሰልፈውና ዋጋ ከፍለው በመጨረሻ ደግሞ የበሰበሰው ጭቆና ባለያቸው ላይ ቀጣየ አንዳይሆን መደራጀትና መከላከል አለባቸው። ኢሕአፓ ይህን በተመለከተ ያካሄደው ትግል የሚታወቅ ነው። ሴቶች በድርጅቱ ተሰልፈው መብታቸው ተከብሮ፣ሚናቸው ታውቆ፣ጀግንነታቸው ተደንቆ ታግለዋል። እናቶች በከተማው ትግል ወቅትም ያደረጉት አስተዋፅዖ አስደናዊ ነበር። ወጣት ሴቶች ብዙ መቶና ሺ ወንዶችን እየመሩ በዱር በገደሉ ድሎቸነ አስመዝገበዋል። ይህ ሁሉ የታሪክና የተመክሮ ማህደራችን ግልፅ ያደረገው ሀቅ የኢትዮጵያ ሴቶች የትግሉ ምሰሶ መሆናቸውን ነው። የጅገና እናት ብቻ ሳይሆን የጀግንነት ቋትና መከሰቻ መሆናቸውን ነው።

የቤት እመቤት ብቻ ሳይሆን የትግሉም እመቤት መሆናቸውን ነው:: ልጅ አሳዳጊ የፍቅር ምንጭ እናቶች ቢሆኑም በጠላትላየ ያመረረ ጥላቻን ይዘው በቆራጥነት የሚታገሉ መሆናቸውን ነው:: ትግሉ ነው ህይወቴ ብለው የተሰዉት ሴቶችን ስንዘክርና ዛሬ የትግል አባወራ ነን ሱሪ ለብሰናል ብለው እየደነፉ ጠላት ሲቆጣ ብረክ የሚይዛቸውን የወረቀት ነብሮች ስናስተያይ ሴቶችን ወደ ትግሉ የመሳቡ ግዳጅ በጣም አጣዳፊ ሆኖ እናገኘዋለን::

ሰማይ በግማሹ አይቆምም::አለ ሴቶች ተሳትፎም ትግል ከግብ አይደርስም:: ኢሕአፓ ትላንት የሀገራችን ጀግኖች ሴቶች አደራጅቶ እንደታገለው ሁሉ ዛሬም ሴቶችን ወደ ትግሉ ለመሳብ ሙሉ ትኩረትን ሰጥቶ መንቀሳቀስ የግድ ነው ይላል:: የኢትዮጵያ ሴቶች ታሪክ ፅፈዋል:: ዛሬም ከበደሉ ክምር ስር የነገን ብሩህ ተስፋ ሲፈነጥቁና ህብረተሰቡን ሲያስስቀጥሉ የምናያቸው እነሱው ናቸው:: ማን ያውራ የታገለ ካልን ደግሞ ወሬውም ታሪኩም ለጀግኖቹ ሴቶች መተው አለበት::

የትምክህትና የጭቆና ገመድ ይበጠሳል!!
ሴቶች መብታቸውን በትግላቸው ያረጋግጣሉ!!